# ኢትዮጵያዊ?!

የትላንት ህልመኛ
የኢትዮጵያ ጠላት አፍራሿ ደመኛ
ዛሬ ተቆራርሳ
ከናቋት ኢትዮጵያ ፣ በአስተዳደር አንሳ
ዘመን ተገልብጦ
መለስ ጦር አዘዘ ፣ ዚያድባሬን በልጦ።
ዜናው ተለፈፈ
"ኢትዮጵያ ወረረች!" ተነዛ ተጻፈ።...
የቷ ናት ኢትዮጵያ?
የነ መለስ እልቢያ?!
በገዳይዋ ወድቃ
ተቆራርሳ ደርቃ ፣
"አለሁ!" ባይዋ ልጇ
ሲታጨድ ከደጇ ፣
"ውስጡን ለቄስ" ሆኖ ፣ ላዩ ብቻ ቢታይ
የልጆቿ አጫጆች ፣ የእራሷም ገዳይ ፣
ዜግነት ረክሶ ፣ "ኢትዮጵያዊ!" ተብለው
"ኢትዮጵያ ወረረች!" ሶማሌን እንበለው?!
በኢትዮጵያማ አለም
ሌላ መውረር የለም!
"የራሷን የማትሰጥ ፣ የሰው የማትነካ
ኢትዮጵያ መሆኗን ፣ አልተረዱም ለካ።"
ይህ ነው የምናውቀው ኢትዮጵያዊ መንፈስ
የራሱን የማይሰጥ ፣ በሰው ላይ የማይደርስ።
ነጥቋት የልጅ ክርዳድ ፣ የራሷን ነጻነት ፣
ዛሬ የጎደለች ፣ እማማ ጥንታዊት ፣...
"ሶማሌን ወረረች ነጻ ልታወጣ ¡ "
ማለት አይጋብዝም ፣ ለፌዝ ለለበጣ?!
ባይሆን የአሁኖቹ ፣ ቆንጆ የአገር መሪ
ሃብታም ለመማረክ ፣ ሌላውን ወራሪ
ክብራቸው አንድ ነው ፣ "ታሪከ - መሰሪ!"።
ምን ይሆን የዛ ህዝብ ፣ የበቀል በደሉ?
እንጨት የሚሳገው በሰሩለት ቁስሉ፤?
የዘሩ ባይሰራ ፣ የጎሳ ተንኮሉ
በእምነት በሃይማኖት ታሪክን ሊያባሉ ፣
"ኢትዮጵያን አትንኩ!" ፣ የነብይ ቃል ወድቃ
በሰው እምነት ጣልቃ ፣ ስንጥር በአገር ላንቃ።
የሚያንገበግበው የሚያቃጥለው ቃል
ሶማሌን ወራሪው ፣ "ኢትዮጵያዊ" ሲባል።

Kefyalew Fente ( zinqekin@yahoo.com ) July22/2006